ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅፅ 34 ቁጥር 5 የካቲት 2001 ዓ.ም

# የካቲት አሁንም ህያው ነው

እንደ መብረቅ አስገምግሞ፥ እንደ ጎርፍ ወሃ ሁሉን አዳርሶ፥ ለራሱ ህይወት ዘርቶና ክንዱን አፈርጥሞ በየካቲት ስድሳ ስድስት ብቅ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ያንን ለዘመናት በሕዝብ ላይ ግፍና በደል ሲፈጽም የኖረውን የፊውዳል ሥርዓት ገርስሶ ጥሎ በአገራችን ታሪክ አቢይ ምዕራፍ ካስመዘገበ 35 ዓመታትን አስቆጥሯል። በዚያን ወቅት የተወለዱ ዜጎች ዛሬ ልጆች ወልደው ቤተሰብ አፍርተው የሚኖሩ ጎልማሶች ሆነዋል። ከእነዚህ ውስጥ የየካቲትን ገድል የሚያውቀው የታሪክ ምዕራፍን ያገላበጠ ወይም በአፈ ታሪክ የሰማው ብቻ ነው። በዚያን ወቅት በእንቅስቃሴው የተሳተፉትም ሆነ እንቅስቃሴውን ለማየትና ለመከታተል ዕድል አግኝተው የነበሩ በህይወት ያሉ ዜጎች ስለ እንቅስቃሴው አነሳስ፥ ስለ ይዘቱና ጥንካሬው ዛሬ ማስታወስ ቢሳናቸው መርሳታቸው ከዘመን ብዛት የመጣ ስለሚሆን ብዙ ሊፈረድባቸው አይችል ይሆናል። የካቲት ግን እንደአልባሌ ነገር የሚረሳ ወይም ለማስተወሻ በታሪክ መጽሐፍት ተመዝግቦ የሚተው አልሆነም። በየካቲት ስድሳ ስድስት የተከሰተው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ያነሳቸው ዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች ዛሬም መልስ የሚፈልጉ የሀገራችን ችግሮች ናቸው። የየካቲቱ እንቅስቃሴ ተረግዞ እንዲወለድ ምክንያት የሆኑት አበይት ሀገራዊ ጉዳዮች፤ እንቅስቃሴው አበክሮ የጠየቃቸው፥ የታገለባቸው ችግሮች አሁንም ውስጣችንን የሚያብሰለስሉ፥ አእምሯችንን የሚቆረቁሩ፥ የደም ስራችንን የሚነዝሩ በመሆናቸው የየካቲቱ ስድሳ ስድስት እንቅስቃሴ አሁንም ህያው ነው።

ዴሞክራሲያዊ መብቶች እውን ይሁኑ፥ የንግግር የጽሁፍና የመደራጀት መብቶች ይከበሩ መሬት ላራሹ ይሰጥ፥ ሠርቶ አደሮች ተገቢና የኑሮ ውድነትን የሚሸፍን ደመወዝ ይከፈላቸው፥ የኑሮ መሻሻል ይደረግ፥ የዕቃዎች ዋጋ መናር ቁጥጥር ይደረግበት፥ ለሥራ

*አጦች ሥራ ይሰጥ፥ በብሔረሰቦች መካከል ልዩነት አይደረግ፥ የብሔረሰብ ጥያቄዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈቱ፥ የሃይማኖት እኩልነት ይኑር፥ በጾታዎች መካከል ልዩነት አይደረግ የሚሉና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን አንስተው ተማሪዎች፥ መምህራን፥ ሠራተኞች፥ አርሶ አደሮች፥ ወታደሮች፥ ሥራ አጦች፥ ወንዱ ሴቱ፥ ወጣቱ አዛውንቱ፥ እስላሙ ክርስቲያኑ፥ ወዘተ… ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ፥ የሥራ ማቆም አድማ በመምታት፥ ታግለዋል፥ አመጾችን አካሂደዋል፥ መስዋዕትነትንም ከፍለዋል። እንቅስቃሴው በባለ ነፍጥና ፀረ ሕዝብ ቡድን በመጠለፉ ላለፉት 35 ዓመታት የተነሱት መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ሳያገኙ የውሃ ሽታ ሆነው ቀርተዋል። በአምባገነኖች አስከፊና የበደል አገዛዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተባባሱት ችግሮች አገራችንንም ሆነ ሕዝባችንን ከድጡ ወደ ማጡ እየከተቷቸው መሄዳቸውን በገሃድ እያየነው ነው።*

*የንግግርና የጽሁፍ ነፃነቶች ይከበሩ፥ ተቃውሞን በሰላማዊ ሰልፍም ሆነ በሌላ መንገድ የመግለጽ መብት ይረጋገጥ፥ የመደራጀት መብት ይኑር ባጠቃላይም ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ይሰጡ የሚሉና ሌሎችም የየካቲቱ እንቅስቃሴ ያነሳቸው ፖለቲካዊ ጥያቄዎች መልሳቸው የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥን፥ የሕዝባዊ መንግሥት ምሥረታን ጠያቂ ነበር። የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ከሰማይ እንደ መና የሚወርዱ ወይም በአንድ ወይም በጥቂት ግለሰቦች መልካም ፈቃድ የሚቸሩ አይደሉም። በሕገ መንግሥት ሰነድ ላይ ስለሰፈሩ ብቻም በተግባር ውለው የሕዝብን ፍላጎትና ምኞት ሊያሟሉ የሚችሉም አይደለም። ሕዝብ በተግባር በእነዚህ መብቶች ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በመንግሥታዊ ተቋም ላይ የበላይነት ሲኖረው ብቻ ነው። ንብረትነቱ የሕዝብ የሆነ፥ ለሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት የቆመ፥ በሕዝብ የተቋቋመ መንግሥት ሲመሠረት ብቻ ነው። ገለልተኛ መሆን ያለባቸው መንግሥታዊ መዋቅሮችና ተቋሞች ሕዝብን ሳይሆን የተወሰነ ግለሰብን፥ የተወሰነ ቡድንን ወይም የተወሰነ ፓርቲን የሚያገለግሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ ዴሞክራሲያዊ መብት ሊረጋገጥ አይችልም። ተጠሪነታቸው ሕዝብ ለመረጠው አካል ሆኖ አገርንና ወገንን ማገልገል የነበረባቸው የወታደርና የፀጥታ መዋቅሮች የመንግሥትን ሥልጣን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በእጁ ባደረገ ግለሰብ ወይም ቡድን ቁጥጥር ሥር ውለው ለእነዚህ አምባገነኖች መገልገያና መጠቀሚያ ከተደረጉ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይገደባሉ፥ ይጣሳሉ። የየካቲቱ እንቅስቃሴ ያነሳው አቢይ ጉዳይ፤ ሕዝብ የበላይ የሆነበት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት በአገራችን እንዲመሠረት ነበር። እንቅስቃሴው ያለመው ራዕይ ድልን ተቀዳጅቶ ወደ ተግባር ሳይለወጥ በባለነፍጥ ወታደር ተጨናግፏል።*

*የየካቲት 66 እንቅስቃሴ ያዘጋጀውን ርካብ እንደመወጣጫ ተጠቅሞ በሕዝብ ትከሻ ላይ ቂጥጥ ያለው የምርጥ መኮንኖች አምባገነኑ ቡድን ደርግ፥ ሰደድ፥ ኢማሌደኅ፥ ኢሰፓአኮ፥*

*ኢሰፓ በሚል ስም የሚታወቁ አፋኝ ቡድኖችን በመመሥረት፥ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት፥ በኀብረተሰብዓዊነት፤ በኢሕዲሪ ወዘተ...ስም የሚጠሩ የፌዝ የመንግሥት አካሎችን በማቋቋም ፋሽስታዊና አምባገነናዊ የሆነ አገዛዙ ዘርግቶ ለ17 ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ ሲበዘብዝ፥ ሲጨቁን፥ ሲበድልና ደም ሲመጥጥ ቆይቷል። አፋኙንና አስከፊውን አገዛዝ በመቃወም ድምፃቸውን ያሰሙ፥ ትግል ያካሄዱ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች በአረመኔው ቡድን በየአደባባዩ በገፍ ተረሽነዋል፥ አካለ ስንኩላን ሆነዋል፥ በየእስር ቤቱ ማቀዋል፥ አገር ጥለው ተሰደዋል። ለ17 ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያሰቃይ፥ ሲበድልና ሲረሽን ቆይቶም በመጨረሻ ወደ መቃብሩ ተወርውሯል።*

*ደርግ ሲወገድ በመሣሪያ ኃይልና ባዕዳን ድጋፍ ሥልጣን የያዘው የወያኔ ቡድንም መንግሥታዊ ተቋሞችንና መዋቅሮችን በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን ዘርግቶ ሕዝብ የማፈንና የማሰቃየቱን ተግባር ቀጥሎበታል። በመጀመሪያው ወቅት በወሰዳቸው የማስመሰያና የማታለያ እርምጃዎች አንዳንድ ዜጎች ሊደናገሩ ቢችሉም የወያኔ አምባገነንነት ግልጥጥ ብሎ የወጣው ከጥንቱ ከጠዋቱ ነበር። ወያኔ ገና ሥልጣን እንደያዘ ቀድሞ የነበረውን የጦር ኃይል መዋቅር አፍርሶ ለትግራይ ነፃነት ሲታገል በነበረው በብቸኛነት በሚቆጣጠረው ሠራዊት ተክቷል፥ የፀጥታውን መዋቅር አፍርሶ በወያኔ አባላት ቁጥጥር ስር እንዲውል አድርጓል፥ ቁልፍ ቦታዎችን የወያኔ አባላት እንዲይዙት በማድረግ ቢሮክራሲውን ተቆጣጥሯል። የሽግግር ጉባዔ፥ የሽግግር መንግሥት፥ ሕገ መንግሥት፥ ነፃ ምርጫ፥ ነፃ ፕሬስ ወዘተ... የወያኔ አምባገነንነትን ለመሸፈን የተፈጠሩ ጭምብል መሆናቸው ቀደም ብሎ የታወቀ ሐቅ ነበር። ከብዙ ዓመት በኋላም በግንቦት 97 ምርጫ የወያኔ ጋሻ ጃግሬዎች ለመካድና ለማስተባበል በማይችሉበት ደረጃ ሽንፈት ሲከናነቡ ማንነታቸውና ፀረ ሕዝብነታቸው ገሃድ ወጥቷል።*

*የየካቲት ስድሳ ስድስቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዋና ጉዳይ አድርጎ የታገለለት የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ ከ35 ዓመት በኋላ እውን ሊሆን ባይችልም ይህን ክቡር ዓላማ እውን ለማድረግ ሐቀኛ ዜጎች ትግላቸውን በየፊናው አፋፍመዋል። ትግሉ ብዙ ውጣ ውረድ የበዛበት፥ በእበላ ባዮችና አስመሳዮች እንቅፋት ጋሬጣ የተጣለበት፥ ጊዜ ወሳጅና እልህ አስጨራሽ ቢሆንም ግቡን ከመምታት የሚያግደው ምንም ምድራዊ ኃይል እንደሌለ በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል። በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ዋና ዋና የኢኮኖሚ ችግሮች ተወግደው ሕዝባችን ከድህነትና ከጉስቁልና ተላቆ ራሱንና ቤተ ሰቡን አለ ችግር የሚያስተዳድርበት፥ አገራችንም ከኋላቀርነት ራሷን አላቅቃ በእድገት ጎዳና ልትጓዝ የምትችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር የተማሪው እንቅስቃሴ ለረዥም ጊዜ ሲታገልበት የቆየ ጥያቄ መሆኑም ታሪክ የመዘገበው ሐቅ ነው። የየካቲት ስድሳ ስድስቱም አብዮት የኢኮኖሚ*

ጥያቄዎችን አንስቶ ታግሏል፡፡ መሬት ላራሹ ከሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ጀምሮ÷ የደሞዝ ጭማሪ እንዲደረግና የዋጋ ንረቶች እንዲስተካከሉ የሚጠይቁ ጊዜያዊ ጥያቄዎች የእንቅስቃሴው የመታገያ መፈክር ሆነው ትግል ተካሄዶባቸዋል፡፡ ብዙኃኑ አርሶ አደር መሬቱን ተቀምቶ የሚያመርተው ምርት በፊውዳሎች በሚነጠቅበትና የራሱም ሆነ የቤተሰቡ ጉልበት በመሬት ከበርቴዎች በሚበዘበዝበት በገባር ሥርዓት ውስጥ መሬት ላራሹ የሚለው ጥያቄ የኢኮኖሚ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ነፃነትንም የሚመለከት የፍትኅ ጥያቄ ነበር፡፡ ከሕዝቡ 90 ከመቶ የሚሆነው አርሶ አደር ሕዝብ የሚተዳደረው በእርሻ ሥራ በመሆኑ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ችግር ለማስወገድ አርሶ አደሩን ከብዝበዛ ነፃ ማውጣት ወሳኝ ነበር፡፡ ስለዚህም ነው የመሬት ላራሹ ጥያቄ አቢይና ወሳኝ ጥያቄ የነበረውና ዛሬም ቢሆን የአርሶ አደሩ ጥያቄ የሀገራችን የፖለቲካ ጥያቄዎች ሁሉ እምብርትና ዋና ሆኖ የሚገኘው፡፡

በዕቃዎች ዋጋ ንረትና በደሞዝ ዝቅተኛነት ኑሮውን መግፋት ያልቻለው÷ በሥራ አጥነት ተቆራፍዶ የችግር ኑሮውን የተያያዘው÷ በረሃብ እያለቁና በበሽታ እየማቀቁ ያሉ ወገኖቹ ስቃይ ያንገበገበው ሰፊው የኅብረተ ሰብ ክፍል ተጨባጭ ለውጦች እንዲመጡ ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰምቷል÷ ትግልም አካሂዷል፡፡ ችጋርና ረሃብ በየዘመኑ አገራችንን እንዳይጎበኟት ለመከላከልም ሆነ ሕዝባችንን በእርግጥ ከድህነት ለማላቀቅ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ማድረግ አስፈላጊም÷ ግዴታም ነበር፡፡ የየካቲቱ እንቅስቃሴ እዚህ ግብ ላይ ሳይደርስ ፀረ ሕዝብ በሆነ በታጠቀ ቡድን ተጠልፎ ወድቋል፡፡ በተከታታይ ሥልጣን የያዙት አምባገነን ሥርዓቶች አገራችንን በድህነት አዘቅት እያንከባለሏት ልትወጣ የማትችለው ገደል ውስጥ የከተቷት ለመሆኑ ሌላ ምስክር ሳያስፈልግ በአሁኑ ወቅት ሕዝባችን ያለበት የስቃይ ሁኔታን በማየት ማረጋገጥ የሚቻል ነው፡፡

የመሬት አዋጅን በማወጅ ደርግ የገባርነትን ሥርዓት ያስወገደ ቢሆንም በመሬት አዋጁ አርሶ አደሩ የተጠቀመበት ሁኔታ የለም፡፡ መሬትን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የማድረግ እርምጃ አርሶ አደሩን የደርግ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ቁጥጥር ሰለባ አደረገ እንጂ÷ አርሶ አደሩን የመንግሥት ገባር አደረገ እንጂ አርሶ አደሩ ከችግር እንዲላቀቅ፣ ኑሮው እንዲሻሻል የፈየደው ነገር የለም፡፡ የደርጉ መንጋ በሥልጣን በቆየበት የአስራ ሰባት ዓመት የግዛት ዕድሜ ኢትዮጵያ ትቅደም÷ የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም÷ ኅብረተሰባዊነት÷ ማዕከላዊ ፕላን÷ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ÷ የገበሬ ማኅበር÷ የአምራቾች የኅብረት እርሻ (አልማ መልባ ወላንድ)÷ የመንግሥት እርሻ÷ ሠፈራ÷ መንደር ምስረታ፣ ኮታ ወዘተ... የሚሉትን ውጥንቅጥ የሆኑ የኢኮኖሚ ፍልስፍናዎችና ፖሊሲዎችን በየጊዜው ተግባር ላይ ለማዋል እየተፍጨረጨረ አገሪቱ ልትወጣ ከማትችለው ማጥ ውስጥ ከቷት ሂዷል፡፡ በደርጉ የሥልጣን ዘመን የአገሪቱ

ኤኮኖሚ በብዙ ዓመታት ወደኋላ ተንደርድሯል፤ ድህነትና ችግር ተስፋፍቷል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችንም በረሃብና በችጋር አልቀዋል፤ ምጽዋተኞች ሆነዋል።

ለሸንገላ የዴሞክራሲ ካባ አጥልቆ በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን የያዘው የትግራዩ ነፃ አውጭ ነኝ ባዩ የወያኔ ቡድንም ለሥልጣኑ መሠረትና ማገር የሆኑትን ክፍሎች ይጥቀም እንጂ ብዙኃኑን ከድህነትና ከችግር ለማላቀቅ የቻለበት ሆነ የፈለገበት ሁኔታ አይታይም። እንዲያውም የችግሩ ክብደትና መጠን ካለፈው የባሰ ሆኖ የሚገኝበት ሁኔታ ይታያል። ወያኔም እንደደርግ መሬትን በቁጥጥር ስር አድርጎ በአርሶ አደሩ ላይ ያለውን ቁጥጥርና ብዝበዛ አጠናክሮ ይገኛል። በወያኔ ዘመን የሀገሪቷ የተፈጥሮ ሀብት በጥቂት የወያኔ ከበርቴዎች ቁጥጥር ስር ገብቷል። የወርቅ ማዕድኑ ለአላሙዲና ለሸሪኮቹ ሌሎች የማዕድን ሀብቶችም ለወያኔ የግል ኩባንያዎች ተሰጥተው እየተመዘበሩ የሚገኙበት ሁኔታ ነው ። ኤፈርት እና ኤንደቨር በሚባሉ ሁለት ታላላቅ ድርጅቶች አቀናባባሪነት በማዕድን፥ በኢንዱስትሪ፥ በእርሻ፥ በትራንስፖርትና በኮንስትራክሽን ዘርፎች የወያኔ ባለሥልጣኖች የሞኖፖል የንግድ ተቋሞችን አቋቁመው በከፍተኛ ደረጃ የአገሪቱን ሀብት እየዘረፉ ያሉበት ሁኔታ መኖሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ከ3.5 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር በላይ ካፒታል ያላቸው ከ50 በላይ ኩባንያዎች የዚህ ዘረኛ ቡድን ንብረት በመሆን ተቋቁመው የኢትዮጵያን ሕዝብ እየገፈፉ ናቸው። የኢትየጵያን ሕዝብ በመዝረፍ በተገኘ ካፒታል ዛሬ የወያኔ ባለሥልጣናት ያልገቡበት የንግድና የሥራ መስክ አለ ለማለት ያስቸግራል። ተወዳዳሪ የሆኑ ታታሪ ነጋዴዎችን በግፊትና በሻጥር ከንግዱ ዓለም እያስወገዱ ገበያውን በሞኖፖል ለመቆጣጠር የሚያደርጉትም ጥረት በገሃድ የተጋለጠ ነው። ብዙዎቹ የቀድሞ ተጋዳላዮች ዛሬ የናጠጡ ከበርቴዎች ሆነዋል። የወያኔ ባለሥልጣኖችና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ከየቦታው የዘረፉትን ገንዘብ በርከት ያለውን ወደውጭ በማውጣት "ዋስትና" ያለው ቦታ ላይ በማስቀመጥ ከፊሉን ደግሞ በሀገር ውስጥ ለመዝናኛና ለቀጣይ ዝርፊያ በማዋል እየተንደላቀቁ ሲኖሩ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበላው አሮበት፥ በስቃይ በመከራ ሰውነቱን እየፎከተ የሚኖር መሆኑንም አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ነው። ረሃብ ከአገራችን አልጠፋም። ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብም ለም በሆነው ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖረውም ጭምር በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ነው። ከራሷ ተርፎ ሌላውን ልትመግብ ትችላለች እየተባለ ሲነገርላት የነበረችው አገራችን በረሃብ የተጎዱ ልጆቿን በህይወት ለማቆየት ከውጭ ረጅዎች በየዓመቱ የምጽዋት እህል መቀበል ተገድዳለች። አምራች ለመሆን ከሚችለው ዜጋ 70 ከመቶ የሚሆነው ሥራ አጥ ነው። ምንም ዓይነት የወር ገቢ የሌለው ዜጋ በሚሊዮን የሚቆጠር ሲሆን ደሞዝተኛውም የሚያገኘው የወር ገቢ ቤተሰቡንና ራሱን ለማስተዳደር የሚያስችለው አልሆነም። በየቀኑ

እንደርችት ወደላይ የሚተኮሰውን የዕቃዎች የዋጋ ግሽበት ለመቆጣጠር ጭቁኑ ሕዝብ ለፈጣሪው እግዚኦታ ከማሰማት በስተቀር ሌላ መፍትሔ ሊያገኝለት አልቻለም። የወር ገቢ ባለህበት እርገጥ ተብሎ በተወሰነበትና ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑት የምግብ ሸቀጦች ዋጋ በየቀኑ በብዙ እጥፍ (ከ300 ከመቶ - ከ300% - በላይ) እየጨመረ በሚሄድበት ሁኔታ ሕዝቡ እንዴት እየኖረ ነው ለሚለው ጥያቄ በተዓምር በመማቀቅ ነው ከሚለው ሌላ ሊገኝለት የሚችል መልስ የለም።

ሕዝባችን በድህነት መቆራመዱን፥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የድርቅና የረሃብ ሰለባ መሆናቸውን፥ የሥራ አጡ ቁጥር መበርከቱን፥ በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋ ራሱን በሕይወት ለማቆየት በየቀኑ በጉርሻ የሚመጠን የምጽዋት ምግብ በልቶ ማደሩን ወዘተ... ወዘተ... በዓይናችን እያየን የአገራችን ኢኮኖሚ በየአመቱ በ10 ከመቶ፥ በ11 ከመቶ አደገ የሚል ፕሮፓጋንዳ ሲንቆረቆርልን ቆይቷል። ኢኮኖሚው አድጓል፥ የኑሮ መሻሻል ተገኝቷል ለሚሉት የገዥው ቡድን አባላትና የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች እውነታው ከዚህ በተገላቢጦሽ ነው እንላቸዋለን። በመጀመሪያ የሀገሪቱ የሀብት መጠን በየአመቱ አድጓል የሚለውን ትክክል ነው ብሎ ለመቀበል መረጃውን የሰበሰበው ተቋም ከወያኔ ቁጥጥር ነፃ መሆኑን በማያሻማ መንገድ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የወያኔ አምባገነን ቡድን በተለያዩ ተቋሞች ያለው ሙሉ ቀጥጥር ምን እንደሆነ የተገነዘበና አሁን በቅርቡ እንኳ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ተቋም በሃይማኖት ተከታዮች ቁጥርና በብሔረሰብ ስብጥር ላይ ሰበሰብኩ ብሎ ያቀረበው መረጃ ምን ያህል የተዛባ መሆኑን በግልጽ የተረዳ ዜጋ በኢኮኖሚውም መስክ የሚሰበስቡት መረጃዎች ለገዥው ቡድን የፖለተካ ትርፍ ሲባል እየተስተካከሉ የሚዘጋጁ ናቸው የሚል ግምታዊ አስተያየት ቢሰጥ ግምቱ ከእውነቱ ብዙ የራቀ አይሆንም።

ሁለተኛ የስታቲስቲክስ መረጃው ትክክል ነው ብለን ራሳችንን ለማሳመን ብንጥር እንኳ አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ሐቅ፣ የአገሪቱ ጠቅላላ ሀብት መጠን መጨመርና ሕዝብ ከዚህ ተጠቃሚ ሆኖ የመገኘቱ ሁኔታ የተለያዩ መሆናቸውን ነው። የኤኮኖሚ እድገት ተገኘ የሚባለው በሀገሪቷ ውስጥ የሚመረተው ጠቅላላ የምርት መጠን አድጎና በየአመቱ እየጨመረ ከሚሄደው የሕዝብ ቁጥር በልጦ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የምርቱ ተጠቃሚ ሆኖ የኑሮ መሻሻል ሲያገኝ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የሀገሪቱ ጠቅላላ የሀብት መጠን ሊጨምር ይችላል። ከውጭ በእርዳታ ወይም በብድር በሚገኝ ካፒታል ወይም ደግሞ ከውጭ ዜጎች በሚያስተላልፉት ገንዘብ ጠቅላላ ገቢው መጨመርን ሊያሳይ ይችላል። ለምሳሌ የዓለም ባንክ ድርጅትን የአሃዝ መረጃ ልብ ብለን ስንመረምር በፈረንጆቹ 2007 ዓ.ም. ብቻ ከውጭ መንግሥታትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የተገኘውና ወደ አገር ውስጥ የገባው

የእርዳታ መጠን ወደ 2 ቢሊዮን ዶላር ይጠጋል፡፡ በመንግሥት ደረጃ የሚታወቅ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውን ያስገቡት የተጣራ የሥራና የንብረት ገቢ ወደ 172 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ መሆኑን ይኸው የአሃዝ መረጃ ያስረዳናል፡፡ ለነገሩ ኢትዮጵያውያን በየአመቱ ወደ አገር የሚያስገቡት የመንግሥት መዝገብ የማያውቀው ገቢ ወደ 1 ቢሊዮን ዶላር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ ይህ ሁሉ በሀገሪቱ ጠቅላላ ሀብትም በጠቅላላ ምርት መጨመር ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ ብሔራዊ የሀብት ገቢ መጠን መጨመር ተጠቃሚ የሚሆኑት ጥቂቶች ሆነው ሰፊው ሕዝብ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ አስከፊ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚኖር ከሆነ የኢኮኖሚ እድገት ተገኘ ተብሎ ደረት የሚያስነፋ አይሆንም፡፡ ተጨባጩ ሁኔታ  የሚያሳየውም ይህንኑ ነው፡፡

በሥልጣን ያሉት ዘመናዊ ሀብታሞች ትላልቅ ግንብ እያስገነቡ፥ የቤት እቃዎችን ሳይቀር ከውጭ አገር በውድ ዋጋ እያስገቡ የተንደላቀቀ ኑሮ ሲኖሩ ድሀው ግን በቀን አንዴ እንኳን በልቶ ህይወቱን ለማቆየት እየተፍጨረጨረ ያለበት ሁኔታ ገሀድ ከሆነ ቆይቷል፡፡ ያለው የመደብ ልዩነት አሰቃቂ ደረጃ መድረሱ ሐቅ ነው፡፡ ሀገራችን አሁንም በበዝባዥ ሥርዓት የተነሳ ድሀ ናት፡፡ በታህሣሥ 2001 በይፋ የተሰራጨው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ሕዝብ እድገት ዘገባ በእርግጥም አገራችን ምን ያህል ኋላ ቀርና ድሀ እንደሆነች  ያስረዳል፡፡ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች አማካይ ዕድሜ፥ የአገሪቱን የትምህርት ይዞታና እንዲሁም ዜጎች ኑሯቸውን ለመሸፈን የሚያስፈልጋቸውን አማካይ የገቢ መጠን መሠረት አድርጎ አሃዞችን ያጠናቀረው ይህ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘገባ ከ179 አገሮች መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ በእድገት ደረጃ አገራችን 10 የሚሆኑ ድሀ የአፍሪካ አገሮችን ብቻ በመቅደም 169ኛ ሆና ተመድባለች ፡፡ በኢኮኖሚ ወደፊት በገፉት አገሮች  ውስጥ የተሟላ ህክምና በመኖሩና የኑሮ ሁኔታም ከፍ ያለ በመሆኑ፤ ዜጎች በአማካይ የሚኖሩት ከ80 ዓመት በላይ ነው፡፡ በአገራችን ግን 52 ነው--ይህም ከታመነና ይሁን ካልንለት ነው፡፡ በኢኮኖሚ ባደጉት አገሮች ውስጥ ለትምህርት የደረሱ  ዜጎች ሁሉም ማለትም መቶ ከመቶ የትምህርት እድል የሚያገኙ ሲሆኑ በአገራችን ግን የትምህርት እድል እያገኘ ያለው 45 ከመቶ ብቻ ነው፡፡ በአማካይ የዓመት ገቢ መጠንም ያለው ልዩነት የትዬ ሌሌ ነው፡፡ በኢኮኖሚ ገፍተው የሚገኙ አገሮች አማካይ የነፍስ ወከፍ የዓመት ገቢ 77089 የአሜሪካ ብር ሲደርስ የአገራችን ግን በመቶ የሚቆጠር የአሜሪካ ብር ብቻ ነው፡፡ በእርግጥም አገራችን የምትገኝበት ደረጃ አሳዛኝ ሐቅ ይህ ነው፡፡

በአገራችን ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየን ሕዝባችን አሁንም በድህነትና በችጋር እየተጠበሰ የሚኖር መሆኑን ነው፡፡ በየካቲቱ ስድሳ ስድስት ሕዝባችን ከድህነትና ከኋላ

ቀርነት እንዲላቀቅ ትግል የተካሄደባቸው የኤኮኖሚ ጥያቄዎች አሁንም ሕዝባችን የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች ናቸው:: መሠረታዊ የሆኑ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች መልስ ሊያገኙ የሚችሉት ግን የሥርዓት ለውጥ ሲኖር፥ የወያኔ አምባገነን ሥርዓት ተወግዶ በሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲተካ ብቻ ነው:: በብሔርና ብሔረሰቦች መካከል እኩልነት ይስፈን፥ የብሔሮች ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ፥ የሃይማኖት እኩልነት ይኑር የሚሉት አበይት ጉዳዮች የየካቲቱ እንቅስቃሴ ካነሳቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ውስጥ የተካተቱ ናቸው:: ኢትዮጵያ የብዙ ብሔርና ብሔረሰቦች አገር ስትሆን ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያደረጓት ደግሞ ሁሉም ብሔርና ብሔረሰቦች መሆናቸው ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችል አይደለም:: ከውጭ ጠላቶች ተዋግተው ህልውናዋን የጠበቁ ወይም እድገቷን አሻሽለው ለዚህ ያደረሷት አንድ ወይም ሁለት ብሔረሰቦች ሳይሆኑ ሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ዜጎች ናቸው:: ስለሆነም የብሔር ብሔረሰብ ስብጥሯ ለኢትዮጵያ ጌጧ ነው እንጂ ሀፍረቷ፥ ጥንካሬዋ እንጂ ጉድለቷ አይደለም :: የብሔርና የብሔረሰብ ስብጥር ለአገሪቷ ጌጥም ሆነ ጥንካሬ ሊሆን የሚችለው ግን እኩልነት ሲሰፍን በብሔርና ብሔረሰቦች ላይ የሚደርሰው በደል ሲወገድ፥ ሁሉም በወንድማማችነት፥ በእህትማማችነት አንተ ትብስ፥ አንች ትብሽ ተባብለው ባንድነት ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው:: እኩልነት ከሌለ፥ በደል ከከፋ፥ መገፋት ከበረታ ብሶት ይስፋፋል በሕዝቦች መካከል አንድነት ለመፍጠርም አስቸጋሪ ይሆናል:: ከራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ውጭ ምንም ሌላ ነገር የማይታያቸው ከፋፋዮችና ገንጣዮችም የሕዝቡን ብሶት እያራገቡ የመገንጠልን ጥያቄ እንደመፍትሔ ወስደው በሕዝቡ ውስጥ ክፍፍል ለመፍጠር ይጠቀሙበታል:: የሀገርም ህልውና አደጋ ላይ ይወድቃል:: ይህን የተረዱ ዜጎች ናቸው የዓመታቱን የወጣቱን ጥሪ በመስማት የብሔሮች እኩልነት ይስፈን፥ የኤርትራ ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ፥ የሚሉ መፈክሮች በየካቲቱ እንቅስቃሴ ውስጥ በስፋት እንዲስተጋቡ ያደረጉት:: በወቅቱ ክርስቲያኑም እስላሙም የሃይማኖት እኩልነት ይኑር በሚል ሰልፍ አብሮ የወጣው የተለያዩ እምነት ተከታይ የሆኑት ኢትዮጵያውያን በእኩልነትና ባንድነት ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ነው:: በሴት እህቶቻችን ላይ በደል አይፈጸም፥ የጾታ እኩልነት ይኑር የሚል መፈክርን በማንገብ ሴቶችና ወንዶች አብረው የተሰለፉት፥ ድምፃቸውን ያሰሙት ጥያቄው መሠረታዊ የሆነ የሰብዓዊ መብትና የፍትኅ ጥያቄ በመሆኑ ነው::

የብሔርና ብሔረሰብን እኩልነት እውን አድርጎ አንድነትን ለማረጋገጥም ሆነ የሃይማኖትና የጾታ ልዩነትን አስወግዶ ሕዝባችን በሰላምና በአንድነት እንዲኖር መሠረቱን ለመጣል የግድ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት መኖርን ይጠይቃል:: የሕዝቡን ሥልጣን ነጥቆ በሥልጣን የተሰየመው የደርግ አገዛዝ አንድነትን በኃይል ማስጠበቅ በሚል ዘይቤ 17

*ዓመታት ሙሉ 60 ከመቶ የሚሆነውን የአገሪቷን ባጀት/ገንዘብ በጦርነት እያፈሰሰ፥ የኅብረተሰቡ ምሰሶ የሆኑትን ወጣት ወገኖቻችንን በገፍ እያስጨረሰ ቆይቶ በመጨረሻ ኤርትራን አስገንጥሎ፥ አገሪቷን ለጠባቦች አስረክቦ ክምብል ብሎ ወድቋል። የብሔር ጥያቄን አንግቦ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የተደራጀውና ሁኔታዎች አመች ሁነው ሲታዩት ማርሽ ቀይሮና በዘዴ አቋሙን አስተካክሎ ሥልጣን የያዘው የወያኔ ቡድን ችግሩን አባባሰው እንጂ መፍትሔ ሊሰጠው አልቻለም። ሥልጣን በያዘ ማግስት ኤርትራን በይፋ-- ወደብ ይገባታል ለኢትዮጵያ ሳይል እንኳን--ለሻዕቢያ አስረክቧል። በሥልጣን ላይ ለመቆየት የብሔርና ብሔረሰብም ሆነ የሃይማኖት ልዩነቶችን እያራገበና በሌሉበትም አዲስ እየፈጠረ የክፍፍል መረቡን ዘርግቶ ሕዝብን እያመሰ ይገኛል። ጠባብ ብሔረተኛው የወያኔ አምባገነን ቡድን ወደ ሥልጣን የመጣው በሕዝብ ምርጫና ፍላጎት ሳይሆን በጠመንጃ ኃይልና በባዕዳን ድጋፍ በመሆኑና መሠረት የሆኑትም ሆነ አቅፈው ደግፈው ያቆዩት ከአንድ ብሔር የተውጣጡ በቁጥር የተወሰኑ የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች በመሆናቸው በሥልጣን ላይ ለመቆየት የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ መከተል የግድ ሆኖበታል። ይህን ፖሊሲ እውን ለማድረግ ደግሞ በብሔርና ብሔረሰቦች፥ እንዲሁም በተለያዩ የእምነት ተከታዮች መካከል ልዩነትን በመፍጠርና በማራገብ የተደራጀ ወይም የተጠናከረ ተቃውሞን ማዳከም ይኖርበታል። በኦሮሞና በአማራው፥ በትግራዩና በሌሎች ብሔረሰቦች፥ በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች፥ ወዘተ... መካከል ልዩነቱ እንዲሰፋ፥ ግጭቶች እንዲፈጠሩ፥ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲተላለቅ በይፋና በጀርባ በተደረጉ ቅስቀሳዎች የብዙ ወገኖቻችን ህይወት እንደቅጠል ረግፏል። በወተር፥ በአርባ ጉጉ፥ በአሰቦት፥ በአደባባይ ኢየሱስ፥ በአንዋር መስጊድ፥ በአረካ፥ በጎንደር፥ በጅማ፥ በድሬደዋ፥ በጋምቤላ፥ በኦጋዴን፥ ወዘተ... ተከስተው የነበሩትን ሁኔታዎች የምናስታውሳቸው በሀዘን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተሸረበ ያለበትን ተንኮል እየተቋቋመ፥ እየተደረገበት ያለበትን ግፌት እየመከተ አንድነቱን ጠብቆ እስካሁን ቆይቷል።*

*ሰላሳ አምስት አመት ወደኋላ ልቦናችንን መልስን በዐይነ ህሊና የነበረውን ሁኔታ ስንቃኝ ከየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጥንካሬም ሆነ ጉድለት ዛሬ ትምህርት ልንወስድ እንችላለን። የየካቲቱ እንቅስቃሴ ሕዝባዊ ቁርጠኛነትና ወሳኝነት የታየበት እንቅስቃሴ ነበር። የፊውዳሉን አፈናዎችና ማስፈራሪያዎች ተቋቁሞ ቀስ በቀስ እያደገ የሄደ፣ በዋናው ከተማ ተጀምሮ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሌሎች ከተሞችን ያጥለቀለቀ፣ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ያካተተ እንቅስቃሴ ነበር። በተከታታይ በተካሄዱ ሰላማዊ ሰልፎችና የሥራ ማቆም አድማዎች ብቻ የሕዝብ ትብብርና ኃይል ለዘመናት እስከ አፍንጫው በመታጠቅ ኃይሉን አፈርጥሞ የነበረን አምባገነን ኃይል ሊያርበደብድ፥ ሊያዳክምና ሊገረሰስ የሚችል ችሎታ እንዳለው አረጋግጧል። በየካቲት አብዮትም ኢሕአፓ በትግል ተፈትኖ የሕዝብ አለኝታነቱን*

ለማስመስከር መቻሉ መጠቀስ ያለበት ነው። የየካቲቱ እንቅስቃሴ ኅብረ ብሔራዊ ነበር። የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰብ አባላት፥ የተለያየ እምነት ተከታዮች፥ በጾታና በእድሜ የተለያዩ ወገኖች በኅብረት እጅ ለእጅ በመያያዝ የተሳተፉበት እንቅስቃሴ ነው። የሃይማኖት እኩልነት ይኑር የሚለውን ጥያቄ ያነሱት እስላሞችም ክርስቲያኖችም ናቸው፤ የብሔርና ብሔረሰብ እኩልነት ይኑር የሚለውን ጥያቄም አንግበው ትግል ያካሄዱት የአማራ፥ የትግሬ፥ የኦሮሞ፥ የሲዳማ፥ የሱማሌ፥ ወዘተ... ብሔረሰብ አባላት ናቸው። የጾታ እኩልነት ይኑር ብለው ጥያቄ ያቀረቡት ወንዶችም ሴቶችም ናቸው። የኢኮኖሚ ጥያቄዎች የተነሱት በሁሉም ብሔረሰብ አባላት፥ በሁሉም ጾታ፥ በሁሉም የዕድሜ ክልል ነው። የአንዱ ቁስል ሌላው እየተሰማው ሁሉም በአንድነት የታገለበት በእርግጥም የኢትዮጵያዊነት ኅብረ ብሔረዊ ጌጥ ደምቆ የታየበት እንቅስቃሴ ነበር ማለት ይቻላል።

የየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅሰቃሴ አቢይ ጉድለት የተደራጀ ኃይል ሊመራው አለመቻሉ ነበር። የየካቲቱ አብዮት የፈነዳው በግብታዊነት ነው። ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ እንቅስቃሴውን የመራ የተደራጀ ኃይልም አልነበረም። በአብዮታዊ ኃይሎች ተመሥርቶ በሕቡዕ መደራጀት ጀምሮ የነበረውም ኢሕአፓ እንኳ በዚያን ወቅት ገና ጨቅላ ስለነበር አባላቱ በእንቅስቃሴው ውስጥ ጎላ ያለ ሚና ከመጫወታቸው ሌላ እንቅስቃሴውን ሙሉ ለሙሉ ሊመራ የቻለበት ሁኔታ አልነበረም። ስለሆነም የየካቲቱ እንቅስቃሴ መሪ አልባ ሆኖ በሌላ በተደራጀ ባለነፍጥ በደርግ ተጠልፎ ራዕዩ ለጊዜውም ቢሆን ግቡን ሳይመታ ሊጨናገፍ ችሏል። ከየካቲቱ አብዮት ጉድለት ለመማር የምንችለው ጉዳይ ቢኖር ተደራጅቶ መታገል ትግሉን ለድል ለማብቃት ወሳኝ መሆኑን ነው። ተደራጅተን ከታገልን አምባገነንነትን ለማንኮታኮት ጊዜው አጭር እንደሚሆን ጥርጥር የለንም።

መጀመሪያ ላይ እንደጠቀስነው፤ የየካቲት ስድሳ ስድስቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ያነሳቸው ጥያቄዎች፥ ከሀገራችን እንዲወገዱ ትግል ያካሄደባቸው ዋና ዋና የሀገሪቱ ችግሮች አሁንም መፍትሔ ያላገኙ፥ አገራችንንም ሕባችንንም ተብትበው የያዙ ችግሮች ናቸው። ችግሮቹ ሊወገዱ የሚችሉት አምባገነኑ አገዛዝ ሲወገድ ብቻ ነው። የየካቲቱን ጥያቄዎች አንግበን ወኔውንና ኅብረቱን ተላብሰን፥ በመደራጀት ክንዳችንን አጠናክረን ትግሉን ካጧጧፍን ይህ አስከፊ አገዛዝ ሊወገድ የሚችልበት ወቅት ሩቅ ሊሆን እንደማይችል በእርግጠኛነት መናገር እንችላለን።

በትግላችን ዳግማዊ የካቲትን እውን በማደረግ ድልን እንቀዳጅ!!
የሕዝብ ትግል አቸናፊ ነው!!